# #በእንተ #መርዓት #ወመርዓዊ



አዘጋጅ፦ መ/ር በትረማርያም አበባው

## ... #ስለ #እጮኝነት #ክፍል #1 ...

ብዙ ጊዜ በእጮኝነት ጊዜ ሴቷም ወንዱም ጻድቅ ጻድቅ ነው የሚጫወቱት። አቤት ቅድስና፣ አቤት ብፁዕነት፣ አቤት ፍጹምነት.... እረ እረ እረ.... ሁለቱም እንደ ፓለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ ቅስቀሳ መልካም መልካም ነገራቸውን ብቻ ነው የሚያወሯት። [በእጮኝነቱ ጊዜ የሞተ ሰው ግን ይኮነን ይሆን!? ማለቴ አብዛኛው በዚያ ሰዓት ጻድቅ ነው የሚመስለው]። ነገር ግን የእጮኝነት ጊዜ እንዲህ መልካም መልካሙን ብቻ የሚያወሩበት ሳይሆን ያለባቸውን ችግሮችም አብረው እያወሩ ሲጋቡ እንዴት ሊፈቱት እንደሚችሉ እየተወያዩ መቆየት ይገባል።

እጮኝነት እውነተኛ ማንነትን የሚያሳውቁበት ነው እንጂ ጻድቅ ሳይሆኑ ጻድቅ ጻድቅ የሚጫወቱበት አይደለም።በዋናነት እጮኝነት ያለባቸውን ጉድለቶች የሚተዋወቁበት ነው። ይህም በትዳር ጊዜ እነዚያን ጉድለቶች ለመሙላት የስነልቡና ዝግጅት ለማድረግ ይጠቅማል። እጮኝነት ምንድን ነው? ትዳርስ ምንድን ነው? እጮኝነት ለምን? ትዳርስ ለምን? የሚሉ ርእሰ ጉዳዮችን በዚህ ክፍል እንመልከት። መጀመሪያ እጮኝነት ማለት መጠባበቅ ማለት ነው። ይኸውም ከትዳር በፊት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ለትዳር ከመብቃታቸው በፊት እርሷ የእርሱ እርሱ የእርሷ መሆኑን ተማምነው እስከ ሠርጋቸው እለት መጠበቅ ማለት ነው። ትዳር ወይም ጋብቻ ማለት ደግሞ ሁለቱ እጮኛሞች በቁርባን አማካኝነት አንድ የሚሆኑበት ምሥጢር ነው። ማቴ.19፥5 "ስለዚህ ሰው አባቱን እና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል። ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ"። ይላል። ሁለቱ አንድ የሚሆኑት እንዴት ነው ከተባለ አንደኛ በመኝታ አንድ ይሆናሉ ማለት ነው። እርሷ ከእርሱ እርሱ ከእርሷ ውጭ ከማንም ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ ማለት ነው። ሁለተኛው አንድ ይሆናሉ የተባለው ልጅ በመውለድ ነው። ሚስቱ ሴት ብትወልድ ሴቷ የአንቺ ናት ወንዱ የእኔ ነው ብሎ መለየት የለም። ሴትም ሆነ ወንድ የሚወለደው ልጅ የሁለቱም ልጅ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ነው አንድ ይሆናሉ ያለው። ሌላው አንድ ይሆናሉ ያለው ሁለቱም በአንድ ሆነው ያፈሩት ንብረት ይህ የእኔ ይህ የእኔ ሳይባባሉ በአንድነት ይጠቀሙበታልና ነው። እንጂ አካላቸው ተጨፍልቆ አንድ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 እንደሚናገረው ጋብቻ ለምን ያስፈልጋል ከተባለ፡- አንደኛ ዘር ለመተካት ነው።ዘፍ.1፣28 ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ተብሏል። ልጆችም እግዚአብሔር ለወላጆች የሚሰጣቸው ስጦታዎችና በረከቶች ናቸው። ሁለተኛው ለመረዳዳት ነው። ዘፍ.2፣20። እርሱ ቢደክም አይዞህ ብላ አጽናንታ እንድታበረታው እሷ ብትደክም አይዞሽ ብሎ እንዲያበረታት ነው። ሦስተኛው ለአቅልሎ ፍትወተ ሥጋ ነው። አዳም ከገነት ከተባረረ በኋላ ፍትወታት እኩያት ሰልጥነውበታል። ስለዚህ የሰው ልጅ በገነት እያለ የፍትወት ስሜት አይሰማውም ነበር። ከገነት ከወጣ በኋላ ግን ፍትወት እንስሳዊት ሰልጥናበታለች። ከአሥሩ ሕግጋት አንዱ አታመንዝር ነው። ዘጸ.20፣14 ማመንዘር ማለትም በትዳር የአንተ ካልሆነች ሴት ጋር የፍትወት መገለጫዎችን ማለትም መሳሳም፣ በስልክ ወይም በአካል ተገናኝቶ ዝሙት ቀስቃሽ ንግግሮችን መነጋገር፣ ዝሙት ቀስቃሽ አካላዊ ንክኪዎችን ማድረግ የመሳሰሉትን ማድረግ ነው። ይህም ትልቅ በደል ነው። እኒህን ነገሮች ከተጋባህ በኋላ ከሚስትህ ጋር ማድረግ ትችላለህ። ገና ካላገባህት እጮኛህና ከሌላ ሴት ጋር

ግን ማድረግ ፈጽሞ ኃጢአት ነው። ከአሥሩ ትእዛዛት አንዱን ማፍረስ ይሆናል። ይህ በወንጌልም ጸንቷል። ማቴ.5፣28 "ወደሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል" ተብሏል። ከዚህ ላይ ሴት ተብላ የተገለጠችው ከሚስትህ ውጭ ያሉትን ሁሉ የሚያመለክት ቃል ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክብር አሜን ይቆየን።

## #ስለ #እጮኝነት #ክፍል #ሁለት

ሌላው ወደ እጮኝነት ከመግባታችን በፊት ለእጮኝነት ያሰብናት ሴት/ወንድ ከአራቱ ዝምድናዎች ውስጥ የሌለች/ለ መሆኑን መረዳት አለብን። አራቱ ዝምድናዎች የተባሉም።

1) መንፈሳዊ ዝምድና
2) የአሳዳጊ አባትና እናት ዘመዶች
3) የሥጋ ዝምድና
4) የጋብቻ ዝምድና

የምታጫት ሴት ወይም የምታጪው ወንድ ከእነዚህ ዝምድናዎች ውጭ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24ን ይመልከቱ። የሥጋ ዝምድና ማለት የእናትህ እና የአባትህ ዘመዶችን ሁሉ ማግባት አይገባም። ይህም ማለት አክስት፣ አጎት አያት ቅድመ አየት እያለ ይቀጥላል። ይህም ዝምድና እስከ ሰባት ትውልድ ቀጥሎ በስምንተኛው መጋባት ይቻላል።ይህም ማለት ለምሳሌ አንተ እስከ ሰባተኛ የልጅ ልጅ ብታይና ወንድምህም እስከ ሰባተኛ የልጅ ልጅ ቢያይ የመጨረሻው ሰባተኛው የልጅ ልጅህና የወንድምህ ሰባተኛው የልጅ ልጅ መጋባት አይችሉም። በስምንተኛው ግን መጋባት ይቻላል ማለት ነው። የሰባት ትውልድ አቆጣጠሩ፦

1 አንተ ወይም አንቺ

2 እናትህ ወይም አባትህ

3, የእናትህ እናት እና አባት

የአባትህ እናት እና አባት

4, የእናትህ እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት እናትና አባት

የአባትህ እናት አባትና እናት

የአባትህ አባት እናትና አባት

5. የእናትህ እናት አባት እናትና አባት

የእናትህ እናት እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት አባት እናትና አባት

የአባትህ እናት አባት እናትና አባት

የአባትህ እናት እናት እናትና አባት

የአባትህ አባት እናት አባትና እናት

የአባትህ አባት አባት እናትና አባት

6 የእናትህ እናት አባት እናት አባትና እናት

የእናትህ እናት አባት አባት እናትና አባት

የእናትህ እናት እናት አባት እናትና አባት

የእናትህ እናት እናት እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት እናት አባት እናትና አባት

የእናትህ አባት እናት እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት አባት እናት አባትና እናት

የእናትህ አባት አባት አባት እናትና አባት

የአባትህ እናት አባት እናት አባትና እናት

የአባትህ እናት አባት አባት እናትና አባት

የአባትህ እናት እናት እናት አባትና እናት

የአባትህ እናት እናት አባት እናትና አባት

የአባትህ አባት እናት አባት እናትና አባት

የአባትህ አባት እናት እናት አባትና እናት

የአባትህ አባት አባት እናት አባትና እናት

የአባትህ አባት አባት አባት እናትና አባት

7)_______________

ወንድ ከሆንክ የምታገባት ሴት፣ ሴት ከሆንሽ ደግሞ የምታገቢው ወንድ ትውልዳችሁ ሲቆጠር በሰባቱ ትውልዶች በየትኛውም አቅጣጫ ማለቴ በእናትህ እናት እናት፣ ወይም ባጭሩ ከላይ በጠቀስናቸው ዝርዝሮች ውስጥ እስከ ሰባት ባለው ተመሳሳይ አያት ሊኖራችሁ አይገባም። እህት ወንድም፣ አክስት አጎት ወዘተ በላይኛው ይቆጠራል። ለምሳሌ የአጎትህን ልጅ የማታገባበት ምክንያት ስትቆጠር አንድ አንተ አለህ። ከዚያ በሁለተኛ አባትህ ወይም እናትህ አሉ። ከዚያ በሦስተኛ የእናትህ እናትና አባት ወይም የአባትህ እናት እና አባት አሉ። በሦስተኛው አያታችሁ ስለምትገናኙ መጋባት አይቻልም። በእንደዚህ ዓይነት አቆጣጠር እስከ ሰባት ባለው በሆነ አያት ወይም ቅድመ አያት የምትገናኙ ከሆነ የሥጋ ዝምድና ስላላችሁ መተጫጨት መጋባት አይገባም። የክርስትና አባት ወይም እናት ዝምድና ያልነው ደግሞ መንፈሳዊ ዝምድና ይባላል። መንፈሳዊ ዝምድና የሚባለው ደግሞ አንተን ክርስትና ያነሳህ ሰውየ ሥጋዊ ዘመዶቹ ሁሉ በመንፈሳዊ ዝምድና የአንተ ዘመዶች ይሆናሉ። ስለዚህ የክርስትና አባትህን ዘመዶች በሙሉ ማግባት አይቻልም ማለት ነው። የአሳዳጊ እናት ወይም አባት ዝምድና የተባለው ደግሞ አሳዳጊህ እንደ አባት ወይም እናት ስለሆኑ የአሳዳጊህ ዘመዶች በሙሉ በሥጋ ባይዘመዱህ እንኳ ዘመዶችህ ይሆናሉና ከዚያ አትጋባ ማለት ነው። የጋብቻ ዝምድና የሚባለው ደግሞ አንተና ሚስትህ በዝሙት ምክንያት ብትፋቱ እና እንደገና ሌላ ሚስት ለማግባት ብትፈልግ በሦስቱም ዝምድናዎች በኩል የሚስትህ ዘመድ ያልሆነች መሆን አለባት ማለት ነው። በንሥሓ አባት አንድ የሆኑ ልጆች ከላይ በጠቀስናቸው ዝምድናዎች ካልተዛመዱ በስተቀር መጋባት ይችላሉ። ይህ በሐዲስ ኪዳን በፍትሐ ነገሥት

የቀረበው ዝምድና ነው። የመንፈሳዊ ዝምድና እስከም የለው ብዙ ነው ካለ በኋላ አንድም እንደሥጋዊው ዝምድና እስከ ሰባት ነው ተብሎ ታትቷል። ይህም ቤተክርስቲያን ሰውን ለማዛመድ የሄደችበት ርቀት እጹብ እጹብ ብለን እንድናደንቅ ያደርገናል።

።

## #ስለ #እጮኝነት #ክፍል #3

የእንጀራ እናትህን/አባትህን ልጅ ምንም እንኳ በእናትም በአባትም ባትገናኙም ማግባት አትችልም። ምክንያቱም የጋብቻ ዝምድና ይፈርሳልና ነው። በእጮኝነት ጊዜ ሌላው ትልቁ ጉዳይ የእድሜ ጉዳይ ነው። ፍትሐ ነገሥት ሴት 12/15 ዓመት ሳይሞላት ወንድ 18/22 ዓመት ሳይሞላው ማግባት አይገባውም ይላል። እጮኛ ልያዝ ቢል እንኳ እድሜው ከዚህ ዓመት በታች ከሆነ በቤተሰቡ ፈቃድ እንጂ እርሱ ራሱ መርጦ ማጨት አይችልም። ነገር ግን ይላል ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ሴቲቱ በምኞት አድጋ በአካል የጠነከረች ከሆነ ቢያንስ በ12 ዓመቷ ታግባ ይላል። ከዚያ በታች ግን ማግባትም ማጋባትም አይቻልም። ወንዱም በምኞት ያደገ በአካል የጠነከረ ከሆነ በ18 ዓመቱ ማግባት ይችላል። ከዚያ በታች ግን አይቻልም። ወንዱ ወይም ሴቷ በቤተሰብ ሥር የሚተዳደሩ ከሆነ በቤተሰብ ፈቃድ ያጫሉ። ነገር ግን ራሳቸውን የቻሉ በአካል የጠነከሩ ከሆኑና በኑሮም በቤተሰቦቻቸው ጥገኛ ያልሆኑ ከሆነ ራሳቸው መርጠው ራሳቸው አጭተው ሽማግሌ አስልከው መጋባት ይችላሉ።የእድሜ ጉዳይ መነሻውን ተናገርኩ እንጂ ከዚያ በላይ ከሆኑ ፈቅደው ተፈቃቅደው መጋባት ይችላሉ። በእድሜ ወንዱ ሊበልጥ ይችላል። ሴቷም ልትበልጥ ትችላለች። ነገር ግን እድሜያቸው ተቀራራቢ ቢሆን ይመረጣል። ይኸውም መረዳዳት የሚለውን በሀሳብም ለመረዳዳት የእድሜ መቀራረብ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ዙሮ ዙሮ ግን በፍትሐ ነገሥቱ እንደምናየው የሴቷ አነስ ቢል የተሻለ ነው። ሴት 65 ዓመት ከሆናት በኋላ ማግባት አይገባትም። ሌላው በእጮኝነት ጊዜ ወደፊት ምን ሠርተው እንዴት ሠርተው ራሳቸውን እንደሚያኖሩ ማሰብ መወያየት ይገባል። ሌላው ነገር ደግሞ ለእጮኝነት ለመጠየቅ ሴትም ወንድን መጠየቅ ትችላለች። ወንድም ሴትን መጠየቅ ይችላል። ነገር ግን ከተጠያየቁ በኋላ ሽማግሌ ወደ ቤተሰብ የሚልክ ወንዱ ነው። ወንዱ ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ነው እንጂ ሴት ወደ ወንድ ቤተሰብ ሽማግሌ ልካ "ላገባው ነው" ማለት አይገባትም። ከእጮኝነት በኋላ ጥሎሽ ወይም ማጫ የሚሰጥ ደግሞ ወንድ ነው። ይኸውም ለአዳም መላእክት ወርቅ እጣን እና ከርቤ አምጥተው ሰጥተውታል። አዳምም ለሔዋን ማጫ አድርጎ ሰጥቷታልና የዚያ ምሳሌ ነው።

።

የልጆቻችንን ከርስ ብቻ የምንሞላ ከሆንን እያሳደግን ያለነው ሮሆቦት እንጂ ሰው አይደለም። ከሮሆቦት የተሻሉ ልጆችን ማሳደግ ከፈለግን የተፈጠሩበትን ዓላማ እንዲያውቁ በስነልቡና ጠንካራ እንዲሆኑ በስነ ምግባር የታነጹ ልጆች እንዲኖሩን ከፈለግን ከልጅነታቸው ጀምረን ነገረ እግዚአብሔርን ሃይማኖትን ልናሳውቃቸው ይገባል። እኛ ሆዳቸውን ልብሳቸውን ብቻ እየቻልን አእምሯቸውን ግን በሌላ ሰው ሌላ ትምህርት ካስያዝነው እንደ ስልክ እኛ ቻርጅ እናደርጋለን ሶፍት ዌሩን ሌላ ባዕድ ይሞላዋል ማለት ነው። ሲጀምር ቤተክርስቲያን አንድን ልጅ አንዱ ክርስትና እንዲያነሳው ሥርዐት የሠራች የሃይማኖትን ትምህርት ጠንቅቆ እንዲያስተምረው ነው። አሁን አሁን ግን ይህ የለም። ነገር ግን የትዳር ዋናው ዓላማ የእግዚአብሔርን አምሳል የሆነ ልጅን ማስገኘት ነው። ስለዚህ ልጆቻችን በመሰረታዊነት

ከምግበ ሥጋም ከልብሰ ሥጋም በተጨማሪ የሚያስፈልጋቸው ምግበ ነፍስ ነው። ስለዚህ በልጅነታቸው ቤተክርስቲያን እየወሰድን እናቆርባቸዋለን አበ እመ ማለት ሲጀምሩ ደግሞ በቃለ እግዚአብሔር አፋቸውን እናስፈታቸዋለን።እንግዲህ በትዳር አማካኝነት ባልና ሚስት የእግዚአብሔር አምሳል የተባለውን ሰው ያስገኛሉ። ይህም ትልቅ በረከት ነው።1ኛ ዮሐ.2፤13 "...ልጆች ሆይ አብን አውቃችኋለና እጽፍላችኋለሁ" ተብሏል። ሃይማኖትን ማሳወቅ ይገባል።

# #ስለ #እጮኝነት #ክፍል #4

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ሀብታም ወንድ ድሃ ሴትን አላገባም አይበል፣ ሀብታም ሴትም ድሃ ወንድን አላገባም አትበል። ባዕል መለኮት ነዳይ ሥጋን ተዋሕዷልና። ልዑል መለኮት ትሑት ሥጋን ተዋሕዷልና። እንዲያውም ሀብታሙ ወንድ ድሃይቱን ሴት ቢያገባ ሀብታሚቱም ሴት ድሃውን ወንድ ብታገባ ትልቅ ክብር ያገኛሉ። የእጮኝነት መሠረቱ ጾታዊ ፍቅር ነው። ይህም በመፈላለግ ይገለጣል። በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት መካከል የመፈላለግ ስሜት ካለ ሁለቱ ለእጮኝነት መጠያየቅ ይችላሉ። ነገር ግን ፍላጎቱ የአንዱ አካል ብቻ ከሆነ እና አንደኛው የማይፈልግ ከሆነ የፈለግሁትን ካላገኘሁ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ማስቸገር አይገባም። ጠይቆ እምቢ ከተባለ ያው ኃፍረቱን ተከናንቦ ሌላ ይፈልግና ይጠይቅ። ምንስ ቢሆን እርሱ እየወደዳት እርሷ ባትወደው ወይም እርሷ እየወደደችው እርሱ ባይወዳት ከማትወደው/ከማይወዳት ሰው ጋር ለምን ለመኖር ይመኛል። አገባብስ እርሷም እርሱም ተዋደው ሲጋቡ ነው።አንድ ጊዜ አንዱ ጓደኛየ አንዷን ልጅ ፈለገና ሂዶ ጠየቃት ከዚያ እምቢ አለችው። ከዚያ ወረብ ሲያጠና "ንዒነ ብእሲቶ (ሚስቱን ትቶ)" የሚለውን ወረብ ደጋግሞ ይወርብ ጀመር። መምህራችን ልጅቱ እምቢ እንዳለችው ሰምተው ኖሯል። በቃ እሱኛውን ወረብ በትክክል ብለኸዋል ወደቀጣዩ እለፍ አሉት። አንድን ወረብ አጥንተህ በደንብ ከያዝከው ከዚያ ቀጣዩን ወረብ ታጠናለህ። የየኔታ ንግግር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ነው። የመጀመሪያው ወረቡን ብለኸዋል ወደ ቀጣዩ እለፍ ማለታቸው ነው፡ ሁለተኛው ደግሞ በቃ የመጀመሪያ ጥያቄህን ያቀረብክላት ልጅ እምቢ ካለች ወደቀጣዩ እለፍ ማለት እርሷን ትተህ ሌላ ፈልግ ማለታቸው ነበር። ሀብታም ወንድ ሀብታሟን ሴት ድሃ ወንድ ድሃዋን ሴትም ማግባትም ይችላል። ሌላው በእጮኝነት ጊዜ በሐሳብ ያለመስማማት ነገር ካለ ቢለያዩ ኃጢኣት አይሆንም። ከተጋቡ በኋላ ግን መለያየት አይቻልም። የእጮኝነት ጊዜ ለየብቻቸው ነው መኖር ያለባቸው። እጮኛሞች እስካልተጋቡ ድረስ በአንድ ላይ መተኛት በአንድ ላይ ማደር አይገባቸውም።

## #ስለ #እጮኝነት #ክፍል #5

አንድ ወንድ አንዷት ሴትን ለማግባት ወይም አንድ ሴት አንድን ወንድ ለማግባት የግድ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶች አሉ። ከእነዚህም አንዱና ዋናው ሃይማኖት ነው። ሴቶች በሃይማኖት የማይመስላችሁን ወንድ አታግቡ። ወንዶችም እንዲሁ በሃይማኖት የማትመስላችሁን ሴት አታግቡ። ታድያ እንዲህ ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ.7፣14 "ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሷል። ያላመነችም ሚስት በባሏ ተቀድሳለች" ይላልሳ ምን ማለት ነው? ካልከኝ። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተነገረበትን ምክንያት ማወቅ ሀሳቡን በትክክል እንድንረዳው ያደርገናል። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለው አሕዛብን አስተምሮ ወደ ክርስትና ሲመልስ ሚስት ክርስቲያን ትሆንና ባል ሳይሆን ይቀራል። ባል ክርስቲያን ይሆንና ሚስት ሳትሆን ትቀራለች። በዚህ ምክንያት ጠብ እንዳይነሳ ባል ክርስቲያን ከሆነ በጊዜ ሂደት አስተምሮ ክርስቲያን ያደርጋታል በማለት ይህንን ተናገረ። ይህንንም የሚያስረዳን ቁጥር 13 ላይ "ሴቲቱም የማያምንና ሚስቲቱን የሚያፈቅር ከእርሷም ጋር ሊኖር የሚወድ ባል ቢኖራት ባሏን አትፍታ" ይላል። የሚያፈቅራት ብሎ የገለጠው የሚወዳት ከሆነ ለእርሷ ሲል ትንሽ ቆይቶ እንደ እርሷ ሃይማኖት ይሆናልና እንዲህ አለ። ነገር ግን ተምሮም ተነግሮም ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ካልመጣ ልትፈታው እንደሚገባ ቅዱስ ጳውሎስ ከዚሁ ምእራፍ ቁጥር 15 ላይ "የማያምን ግን ቢፈታ ይፍታ" ብሎ ነግሮናል። ይህንን መነሻ አድርገው 318ቱ ቅዱሳን ሊቃውንት ደግሞ በፍትሐ ነገሥታቸው ክርስቲያን ክርስቲያንን ብቻ እንዲያገባ ሥርዐት ሠርተዋል።

።

ስለዚህ አሁን ላይ አስተምረህ ወደ ሃይማኖት ከመለስክ በኋላ አጭተህ ማግባት ትችላለህ እንጂ ገና ወደ ትክክለኛዋ ሃይማኖት ሳትመጣ እያለች እርሷን አግብቼ ወደ እኔ ሃይማኖት እመልሳታለሁ ግን አትበል። ሥለዚህ ባልና ሚስት በሃይማኖት አንድ የሆኑ መሆን አለባቸው። በሃይማኖት አንድ ሆነው ከተጋቡ በኋላ ከሁለት አንዱ ሃይማኖቱን ቢቀይርሳ እንዴት ይሆናል የሚል ጥያቄ ከጠየቅከኝ ደግሞ መልሱ "ይፋቱ" ነው። ምክንያቱም በወንጌል ማቴ.10፣37 "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ይላልና ነው። ከዚህ ጥቅስ በታች ቁጥር 34 ላይ "ሰይፍን እንጂ ሰላም ለማምጣት አልመጣሁም" ብሏል። የዚህ ትርጉሙ በሃይማኖት ምክንያት እናትና አባት ባልና ሚስት ወላጅና ልጅ ቢለያዩ የሚገባ መለያየት መሆኑን ነው። ሰይፍ የተባለውም ይህ ነው። ከዚህ ላይ "ሰላም" ለማምጣት አልማጣሁም ያለው "አንተም በሃይማኖትህ አንቺም በሃይማኖትሽ ተባብለው በአንድ ተስማምቶ መኖርን ነው ሰላም ያለው"። ይህ ሰላም ክርስቲያናዊ ሰላም አይደለም። ክርስቲያናዊው ሰላም ከክርስቶስ ጋር በመኖር በክርስቶሳዊ ሕይወት በመኖር የሚመጣ ሰላም ነው። ይህኛውን ሰላም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ.14፣27 "ሰላሜን እሰጣችኋለሁ"

ብሎናል። ስለዚህ በሃይማኖት የማይመስለንን ሰው ማጨት ማግባት አይገባም። ከተጋባን በኋላ ሃይማኖቱን ቢለውጥ እንኳ መፋታት ይገባል ማለት ነው።

## #ስለ #እጮኝነት/ትዳር #ክፍል #6

ጋብቻ በሁለት መንገድ ይፈጸማል። አንደኛው ሁለቱም ክብረ ንጽሕናቸውን ጠብቀው ድንግልናቸውን ጠብቀው የሚጋቡ ከሆነ በተክሊል ይጋባሉ። እዚህ ላይ አጥብቀህ ያዝልኝማ ወንድማለም። አሁን አሁን ብዙ እጮኛሞች ከዚህ ቀደም ከሌላ ሳይገናኙ ነገር ግን እርስ በራሳቸው በእጮኝነት ጊዜያቸው ግንኙነት ይፈጽሙና በተክሊል ካልተጋባን ይላሉ። ይህ ፈጽሞ ስህተት ነው። ምናልባት በትምህርት ማጣር ምክንያት አንዳንድ ካህናት ይህንን ብለዋችሁ ከሆነም ከመምህራን ጋር አገናኟቸው። ተክሊል ጋብቻ እስከተፈጸመበት ጊዜ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለቆዩ ብቻ ነው የሚደረገው። ይኸውም የክብራቸው መገለጫ ነው። እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባን ሌላው ነገር ምናልባት በሥራ ብዛት ወይም በሕክምና (ለምሳሌ ድንግልናን ሊያስፈርስ የሚችል ልዩ ኦፕሬሽን የሚደረግ በሽታ) ምክንያት ከወንድ ጋር ሳይገናኙ እንዲሁ ድንግልናቸው የጠፋ ሴቶች ካሉ በተክሊል መጋባት ይችላሉ።ተክሊልን ፍጹም የሚያደርገው ቁርባን ነው። ሁለተኛው የጋብቻ አፈጻጸም ደግሞ ተጋቢዎቹ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፏቸው ወይም በተለያየ ምክንያት ድንግልናቸውን አጥተው የነበሩ ከሆኑ በጸሎተ መዓስባን በቁርባን ይጋባሉ። ነገር ግን ከሁለት አንዳቸው ድንግል አንደኛው ደግሞ ድንግል ያልሆነ ከሆነ። ድንግል ለሆነው ተክሊል ይደረግለታል። ድንግል ያልሆነው ደግሞ ያለ ተክሊል ይጋባሉ። ስለዚህ በድፍረት ተክሊል ባናደርግ መልካም ነው። ይህንን የምታደርጉ ካህናት ካላችሁም ሥርዐተ ቤተክርስቲያንን እያፈረሳችሁ ነውና አምላከ ሥርዐት እግዚአብሔርን ፍሩ። በጾም ወቅት ጋብቻ አይፈቀድም። ጋብቻ ያለ ሥጋው ወደሙ አይሆንም። ያለ ቁርባን የተደረገ ጋብቻ ቁጥሩ ከዝሙት ነው ብለዋል ሊቃውንት በሐተታቸው። ስለዚህ በሐገራችን በተለያዩ ተጽእኖዎች ምክንያት ያለ ቁርባን የሚጋባው ሰው ብዙ ስለሆነ ይህንን ግንዛቤ በመስጠት ካህናት የድርሻቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል። ያለቁርባን የሚደረግ ጋብቻ ቁጥሩ ከዝሙት ነው።በዚህ ዙሪያ ያው አሁን በሀገራችን በገጠሪቱ አካባቢ ባለማወቅ እና በግራኝ መሐመድ ተጽእኖ አብዛኛው ሰው ዝም ብሎ ያለ ቁርባን የተጋባ ነው። እንግዲህ ይህ ባለማወቅ የሆነ ስለሆነ ባለፈው ፈጣሪ ይቅር ይለን ይሆናል የሚል ግላዊ ምልከታ አለኝ። ከአሁን በኋላ የሚደረጉ ሰርጎችን ግን ይህንን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ሁሉም በቁርባን በተክሊል እንዲጋባ የተቻለንን እናድርግ። ባለፈው ይቅር ይበለን። ለወደፊቱ ደግሞ ይጠብቀን።

## #ስለ #እጨኝነት/ትዳር #ክፍል 7

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ፍቺ የሚፈቀድባቸው ምክንያቶች፡-

1) በዝሙት ምክንያት

2) በሃይማኖት ምክንያት

3) ባሏን/ሚስቱን ልታስገድለው/ሊያስገድላት በበቂ መረጃ ከተደረሰባት/ከተደረሰበት ናቸው። አንድ ወንድ ሚስቱን ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት እየፈጸመች ተኝታ ቢያገኛት መፍታት ይችላል። ተናዶ በእርሷ እና ከእርሷ ጋር ተኝቶ ባገኘው ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም። በሃይማኖት ምክንያት የሚለውን ከዚህ ቀደም አይተናል። ከላይ ባሉት ሦስት ምክንያቶች ከሚስቱ የተፋታ ካህን ቢሆን ሌላ ሳያገባ ቢቀጥል ክህነቱ ይቀጥላል። ነገር ግን ሌላ ካገባ ወይም በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ካገኛት በኋላ አብሯት የሚኖር ከሆነ ክህነቱ ይሻራል። ካህን በማንኛውም ምክንያት ሁለተኛ ካገባ ከክህነቱ ይሻራል። ክህነቱን አፍርሶ እንደገና ያገባት ሴት ብትሞትበት ግን ሦስተኛ እንዲያገባ አይፈቀድም። ካገባም እንደ አረሚ ይሁን ተብሎ ተነግሮበታል። ምእመን ሚስቱ ብትሞት ሌላ ያገባል። ያች ያገባት ብትሞትም እንደገና ቢያገባ ይፈቀድለታል። አራተኛ ግን ማግባት አይችልም። የምእመን አራተኛ የካህን ሦስተኛ እንደ አረሚ ይሁኑ ተብለዋልና። እስከዛሬ ባለማወቅ አድርገነው ከሆነ ለወደፊቱ እንጠበቅ።ከላይ ከተቀመጡት ምክንያቶች ውጪ ግን ማለትም ያለዝሙት ምክንያት፤ ሃይማኖት ሳይለውጡ፣ በማስገደል ሂደት ካልተገኙ በሌላ ምክንያት መፋታት አይቻልም። ጸባዩዋ ከፋ፣ ሰነፈች፣ ውበቷ ጠፋ፣ አረጀች፣ ወዘተ ብሎ መፍታት አይቻልም። እስከ እለተ ሞትህ ልትጠብቃት ይገባል እንጂ። ከላይ ካሉት ከሦስቱ ምክንያት ውጭ ሚስትህ ብትበድልህ እንኳ ያንን ታጋሽ ሆነህ አረጋግተህ በፍቅር ልትኖሩ ይገባል። የሚደርስብህን በደል ሁሉ ችለህ ኑር። ሴቷም ከላይ ካሉት ምክንያቶች ውጪ ከሆነ የሚደርስባትን በደል ሁሉ ታግሣ ትኑር።በሆነ አጋጣሚ ሚስት ወይም ባል የአካል ጉዳተኛ ቢሆኑ እንኳ እስከ መጨረሻው በፍቅር ሊኖሩ ይገባል እንጂ በዚህ ምክንያት መፋታት አይገባም።

## #ስለ #እጮኝነት/ትዳር #ክፍል #8

ከጋብቻ በኋላ ባልና ሚስት ሩካቤ ሥጋ በማይደረግባቸው እለታት ግንኙነት ማድረግ አይገባቸውም። ግንኙነት የማይፈቀድባቸው እለታትም፡-

1) በወር አበባዋ ወቅት

2) ከወለደች ጀምሮ እስከ ክርስትና

3) በእርግዝናዋ ወቅት።

እርግዝናዋ ከታወቀበት ስአት  በኋላ ግንኙነት የሚያደርግ ወንድ ሚስቱ የጸነሰችው ወንድ ከሆነ ግብረ ሰዶም ሴት ከሆነች ከልጁ ጋር ግንኙነት እንደፈጸመ ይቆጠርበታልና ብለው ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት በሐተታቸው አስቀምጠዋል። ነገሩን የማይገባ መሆኑን አክፋፍቶ ለመናገር የተጠቀሙት ቃል ነው።

።

4) ከሁለት አንዳቸው ከቆረበ ከመቁረቡ በፊት ባሉት 3 ቀናት እና ከቆረበ በኋላ ባሉት 2 ቀናትም ግንኙነት ማድረግ አይገባም።

።

5) በአጽዋማትና በዐበይት በዓላት ጊዜ።

ከእነዚህ እለታት ውጪ ግን ሚስት ወይም ባል ግንኙነት ማድረግ ፈልገው አንዱ እምቢ ማለት የለበትም። የእርሱ አካል የእርሷ የእርሷ አካል የእርሱ ሆኗልና። ፈቃዱን ወይም ፈቃዷን ይፈጽምላት/ ትፈጽምለት እንጂ። ሌላው ቀርቶ ንሥሓ አባት ቀኖና ቢሰጥ እንኳ ሚስት ባልን ባል ሚስትን አሳውቆ መሆን አለበት። ሚስት ወይም ባል ንሥሓ ላይ እንዳሉ ከታወቀ ግን ንሥሓሃቸውን እስኪጨርሱ ከግንኙነት ይከልከሉ። ከዚያ ውጭ ግን መከልከል የለባቸውም። ወንዱ ግንኙነት ማድረግ ፈልጎ ሴቷ እምቢ ብትለው እና ሴቷ ግንኙነት ማድረግ ፈልጋ ወንዱ እምቢ ቢላት እናም በዚህ ምክንያት ፍትወት አናዶት ወንዱ ከሌላ ሴት ሴቷ ከሌላ ወንድ ብትደርስ በደሉ የጋራ ነው። የእሱ በደል የእሷ የእሷ በደል የእርሱ ይሆናል።ባልና ሚስት ግልጽ መሆን አለባቸው። ፈቃዳቸውን በግልጽ ሊነጋገሩ ይገባል። ሚስት አካሏን ሳይቀር ለባሏ ከሰጠች ባልም አካሉን ሳይቀር ለሚስቱ ከሰጠ ከዚህ የበለጠ ምሥጢር ምን አለ? ምንም። ስለዚህ ያለመጣጣምና ያለመስማማት ነገሮች ካሉ በግልጽ ሊነጋገሩ ይገባል።ብዙ ሴቶች በሕገ ወጥነት መንገድ ከሌላ ወንድ ይጸንሱና መጽነሳቸውን ወላጆቻቸው ወይም ይህን ጉዳይ የሚፈሩት ሰው እንዳያውቅ ብለው በማሰብ ጽንሳቸውን

በድብቅ ያስወርዱታል። ይህ ግን ሁለት ታላላቅ በደሎችን የያዘ ነው። አንደኛው ባሏ ካልሆነ ሰው ጋር በመገናኘቷ ከአሥሩ ትእዛዛት አንዱ የሆነውን ዘጸ.20፤14 "አታመንዝር" የሚለውን ሕግ ማፍረስ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ዘጸ.20፤13 ያለውን "አትግደል" ያለውን ሕግ መተላለፍ ነው። ስለዚህ ከሌላ ወንድ ጋር ባትገናኙ መልካም ነበረ። ነገር ግን ደግሞ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፏችሁ ግንኙነት አድርጋችሁ ልጅ ቢጸነስ አታስወርዱት ይወለድ። ወላጅ ሰምቶ ያዝናል ብለን እግዚአብሔርን መበደል አይገባምና። ወላጅም ይሁን ወዳጅ ለጊዜው ሊያዝን ቢችልም። ልጁ ተወልዶ አበ እመ ማለት ሲጀምር ግን ኀዘናቸው ይቀንሰል። ሌሎች ደግሞ ግንኙነቱን ፈልገው ግን እንዳይጸንሱ በማለት የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚጠቀሙ አሉ። ይህም ትልቅ ስህተት ነው። ማሕጸን የተፈጠረው ለጽንስ ነው ። ስለዚህ ግንኙነትን መርጦ ልጅ እንዳይወለድ መፈለግ ብዙ ተባዙ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ቸል ማለት ነው። ምናልባት ጸንሰን ወላጆቻችን መጽነሳችንን ሲያውቁ እንዳይቆጡን እንዳያዝኑብን ብለን አስበን ከሆነም ከእግዚአብሔር ሕግ ይልቅ የእናትና የአባትህ ቁጣ የሚያስፈራህ ጣዖት አምላኪ መሆንህን ያሰውቃል። ክልክሉኮ ካላገቡት ሰው ጋር ግኑኝነት ማድረጉ ላይ ነው እንጂ መጽነሱ ላይ አይደለም። መጠበቅ ያለበት መሠረታዊው ሕግ "አታመንዝር" የሚለው ነው። አታመንዝርን ተላልፈሽ መጽነስሽ ለምን ያሳስብሻል። ሁለት በደል መበደል አይገባም። መጀመሪያ ካላገቡት ሰው ጋር ግንኙነት ማድረግ አይገባም። ሁለተኛ ሥጋዊ ፈቃድ አሸንፎሽ ብትሰናከዪ እንኳ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቅመሽ ሁለተኛ በደል አትበድይ።አንድ ጊዜ የፈለገ ሊቃውንት ደብረ ድማህ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የሐዲሳትና የፍትሐነገሥት መምህር የነበሩት የኔታ ወልደ ኢየሱስ መቅጫ "ልጃችንን ወልደነው ምን እናበለዋለን ብላችሁ በመፍራት ገና ከጽንሱ የምታስወርዱ ሰዎች ይህንን ክፉ ሥራ አትሥሩ። ተውት ልጁን ውለዱትና እግዚአብሔር ከገደለው ይግደለው እንጂ እናንተ አታስወርዱ ያሉት ቃል ድንቅ ቃል ነው። ደግሞስ ጽንስን የምናስወርድ ለምንድን ነው? መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በኤልሳቤጥ ማሕጸን እያለ እኮ ነው ጌታን ያመሰገነው። ዮሐንስ ትዝ አይላችሁም እንዴ? ስለዚህ ጽንስን ማስወረድ አይገባም። የተጸነሰው በስርቆት ከሌላ ወንድም ቢሆን መጀመሪያ ትልቅ በደል በድላችኋል። ስለዚህ ሁለተኛ ታላቅ በደል ጽንስን በማስወረድ አትበድሉ።

።

## #ስለ #እጮኝነት/ትዳር #ክፍል 9

ባል ከሚስቴ ጋር ብገናኝ ብሎ ወይም ሚስት ከባሌ ጋር ብገናኝ ምን ችግር አለው ብለው በአደባባይ በሰው መካከል ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድም። በአደባባይ ግንኙነት ቢደረግ ያንን ያየ ሰው በልቡ እንዲመኝ እና አታመንዝር ያለውን ሕግ እንዲሽር ስለሚያደርገው በዚህም ምክንያት እንዳይኮነንብን ነው። ባልና ሚስት የባልና የሚስት ወሬዎችን ማውራት ካለባቸውም እንኳ ልጆቻቸውም ቤተሰቦቻቸውም ጎረቤትም ሳይሰማ መሆን አለበት። ይኸውም ለሚሰማውና ለሚያየው አካል ፈተና እንዳይሆን ነው። በየአደባባዩ መሳሳም እና ፍትወት ቀስቃሽ ድርጊቶችን ማድረግ ግን አንደኛ ባልንጀራን መናቅ ነው። ሌላው በዚያ አካባቢ ያለ ሰው እናንተን ተመልክቶ እንደሚስት አስቡ። ሌላውን ሰው ፈተና ውስጥ የሚያስገባ ራቁትን የሚያሳይ ልብስ ወይም አካልን ጥብቅ አድርጎ በማሳየት የሰውነትን ቅርጽ የሚያሳይ ልብስ መልበስም የርካሽነት ሥራ ነው። የሰው ልጅ ክቡር ነው። ለዝሙት አልተፈጠረም። ዝሙትኮ የሚያኮራ ነገር አይደለም። እንስሳትም የሚያደርጉት ነገር ነው። ከእንስሳት ጋር የሚያመሳስለን ነገር ነው። እና ቢያንስ ከእንስሳት የተሻለ አኳኋን ይኑረን እንጂ። ወይፈንኮ ያረገዘች ላም ካየ አሽቶ ይመለሳል እንጂ አይሰቀልም። ሰው ግን ከወይፈንም አንሶ በእርግዝና ወቅት እንኳ ግንኙነት ካላደረግን ማለት አግባብ አይደለም።ሰው ከዝሙት ውጭ እንዳያስብ እያደረጉ ያሉት ደግሞ ጭፈራ ቤቶች፣ መጠጥ ቤቶች ናቸው። የትውልዱን አስተሳሰብ እያበላሹ ያሉት ደግሞ እኒህ ናቸው። ከእነዚህም በተጨማሪ አሁን አሁን በቴሌቭዥን መስኮት የሚታዩ ድራማዎች፣ ፊልሞች ትውልድ አምካኝ ጅል ትውልድ የሚያፈሩ ናቸው። የሰው ልጅ በፍትወት እንዳይናደድ ከፈለገ አግብቶ ይወሰን። ከዚያ ውጭ ከዚያም ከዚያም መድረስ የመኖርን ዓላማ ካለመገንዘብ የሚመጣ ደዌ ነው።

።

ሌላው ትዳር ፈተና አለበት ይህንን ማወቅ ያስፈልጋል። ትዳር ሀብት ሲጠፋ ውበት ሲረግፍ የሚተውት አይደለም። አብርሃም እና ሣራ ከሀገር ሀገር ሲሰደዱ ኖረዋል። ስደት ቢመጣ፣ ሀብት ማጣት ቢመጣ፣ አካላዊ ጉዳት ቢመጣ እንኳ እስከ መጨረሻው አብሮ በፍቅር መኖር ያስፈልጋል። ሌላው ግን ምራትና አማት አይጥና ድመት ወይም ዓይንና አፈር መሆን የለባቸውም። ብዙ ጊዜ አይስማሙም ለምን እንደሆነ እኔ እንጃ። ነገር ግን ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይሆናል የተባለው ፍትወት ቢነሳበት ወንዱ ከእናቱ ሴቷ ከአባቷ ጋር ግንኙነት ማድረግ አይገባትም ማለት ነው እንጂ ሚስትየዋ የባሏን እናትና አባት ትጥላ ባልዮው የሚስቱን እናትና አባት ይጥላ ማለት አይደለም። ዘጸ.20 እናትና አባትህን አክብር የተባለው እስከመጨረሻው ነው።ምራትና አማትስ መሆን ያለባቸው እንደ ኑኃሚን እና እንደ ሩት ነው። መጽሐፈ ሩትን ከምዕራፍ አንድ ጀምራችሁ ተመልከቱትማ። ሩት ባሏ ሞቶ እንኳ አማቷን ኑኃሚንን አልተወቻትም። እንዲያውም "አምላክሽ አምላኬ ነው። ሀገርሽ ሀገሬ ነው" ብላ ተወልዳ ያደገችበትን ሀገር ትታ ከአማቷ ጋር ተሰዳለች። ጋብቻ መዛመድ ስለሆነ ሴቲቱ የወንዱን ወገኖች ወንዱ የሴቲቱን ወገኖች መውደድና

ማክበር አለበት። ሴቲቱ የባሏን እናትና አባት ራሷን ዝቅ አድርጋ በትሕትና ልታገለግላቸው ልትታዘዛቸው ይገባል። ወንዱም ለሚስቱ አባትና እናት ክብር ሊሰጣቸው ይገባል።ባልና ሚስት አንዱ አንዱን ማስቀናት የለበትም። በፍጹም መከባበር፣ በፍጹም ፍቅር፣ በፍጹም መተማመን ሊኖሩ ይገባል። በባልና በሚስት ማንም ጣልቃ ሊገባ አይገባም። በቤተሰቦቿ/ቹ ወይም በጓደኞቿ/ቹ ተጽእኖ ሚስት ባሏን ልትፈታ ባል ሚስቱን ሊፈታ አይገባም።ባል ወይም ሚስት ልመንኩስ ቢሉ ከተፈቃቀዱ መመንኮስ ይችላሉ። ባሏ ከፈቀደላት ሚስትየዋ መመንኮስ ትችላለች። ሚስቱ ከፈቀደችለት ባልየው መመንኮስ ይችላል። ሚስት ባሏ ሳይፈቅድላት ወይም ባል ሚስቱ ሳትፈቅድለት ግን ልመንኩስ ቢል መመንኮስ አይችልም። ከዚህ ላይ አጥብቀህ ያዝልኝማ አሁን አሁን አንዳንድ ባሕታውያን ነን ባዮች ባልና ሚስትን እያፋቱ ካላመነኮስን ይላሉ። ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ያለ ባሏ ፈቃድ የመነኮሰች ሴት ካለች ከመነኮሰችበት አምጥቶ ከቤቱ ቢወስዳት ምንም ነውር የለበትም። ሚስቱ እንድትመነኩስ ከፈቀደላት በኋላ እሷም ከመነኮሰች በኋላ ሐሳቡን ቀይሮ እንደገና ምንኩስናዋን እንድትተው ቢፈልግ ግን አይቻልም። በምንኩስናዋ ትጸናለች።

## ...........የመጨረሻ ክፍል...........

## #ስለ #እጮኝነት/ትዳር #ክፍል 10

ፈጣሪ የፍትወት ስሜት እንደሚሰማን እያወቀ ለምን አታመንዝሩ ይለናል? የሚል ጥያቄ ይጠየቃል። ለመሆኑ የሰው ልጅ እድሜው ለአካለ መጠን ሲደርስ የፍትወት ስሜት ይሰማዋልና ይህ ተፈጥሯዊ ነው ወይ? ከሆነ እግዚአብሔር ተፈጥሯዊ የሆነን ነገር ተውት ለምን ይለናል? የሚል ጥያቄ ይጠየቃል። ነገር ግን የፍትወት ስሜት ተፈጥሯዊ አይደለም። አዳም ሲፈጠር ፍትወታዊ ስሜትም አብሮ አልተፈጠረበትም። ነገር ግን ሕገ እግዚአብሔርን ሽሮ እፀ በለስን በበላ ጊዜ ፍትወታት እኩያት ሰልጥነውበታል። ስለዚህ ፍትወታዊ ስሜት ተፈጥሯዊ ሳይሆን የድቀት ውጤት ነው። ይህንን በምሳሌ ላስረዳ አንድ ሰው ጤነኛ ሆኖ ከተፈጠረ በኋላ ራሱን ወደ ገደል ቢወረውር እና አካሉ ጎደሎ ቢሆን ይህ አካለ ጎዶሎነቱ በመውደቁ ምክንያት የመጣ እንጂ ተፈጥሯዊ አይደለም። የፍትወት ስሜትም እንዲሁ ነው። ተፈጥሯዊ አይደለም። በአዳም ድቀት ምክንያት የደረሰብን ጉዳት ነው። ይህ ቢሆንም ግን እግዚአብሔር ባወቀ ፍትወታዊ ስሜት ቢሰማን እንኳ ከተፈቀደልን ሰው ጋር ግንኙነት እንድናደርግ የትዳርን መስመር ፈቅዶልናል። ስለዚህም ባል ከሚስቱ ሚስት ከባሏ የሚያደርጉት ግንኙነት ፍትወት አይባልም። ሕጋዊ ግንኙነት ይባላል እንጂ። ለዚያ ነው ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው "ኦ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተጸነስኪ። አላ በሩካቤ ዘበሕግ" ይላል። ድንግል ማርያም ሆይ በኃጢኣት ፍትወት የተጸነስሽ አይደለም። ሐናና ኢያቄም በሕግ ተጋብተው ባደረጉት ግንኙነት ተጸነስሽ እንጂ ይላል። ስለዚህ ሁለቱን ሕጎች ለመጠበቅ ይረዳን ዘንድ ስለ እጮ ኝነትና ስለትዳር በ11 ክፍል ተማምረናል። የቀረውን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ መምህራንን በመጠየቅ ማስፋት ትችላላችሁ።መቼም እግዚአብሔር ያዘዘን ትእዛዛት ሁሉ እኛን የሚጠብቁ ብንጠብቃቸው እኛን የሚጠቅሙን እንጂ ጨቋኝ ሕጎች አይደሉም። ሕጻንን ልጅ እናቱ

ካልበላህ እያለች ስትቆጣው እሱን ልትጠቅመው ነው እንጂ ልትጎዳው እንዳይደለ ማለት ነው። ከአሥሩ ሕግ ደግሞ አንዱ ዘጸ.20፣14 አታመንዝር የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል አንዱ ማቴ.5፣31 "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እርሱ ራሱ አመንዝራ ያደርጋታል የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" የሚለው ነው። ከዚህ ላይ ያለዝሙት ምክንያት ሰነፈች መከነች ወዘተ ብሎ ሚስቱን የሚፈታ ሰው ትልቅ በደለኛ ነው። በዚህ ምክንያት ሚስቱን የፈታን ሰው መልሰው ሊያስታርቁት ይገባል። 1ኛ ቆሮ.7፣10 "ሚስት ከባሏ አትፋታ ከተፋታችም ብቻዋን ትኑር። ያለዚያ ከባሏ ጋር ትታረቅ። ባልም ሚስቱን አይፍታ"። እምቢ አልታረቅም ካለ/ካለች ግን ሊያገቡት/ሊያገቧት አይገባም። አታመንዝር ያለን ሕግም እርሱ ባወቀ እኛን የሚጠብቀን ሕግ ነው። የእኛ ካልሆነች ሴት/ወንድ የሌላ ከሆነች/ከሆነ ሰው ጋር ግንኙነት ለምን እናደርጋለን!? ይህስ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ያፈነገጠ ስለሆነ በነፍስ በሥጋ የሚጎዳን ስለሆነ ልናደርገው አይገባንም። 1ኛ ቆሮ.7፣2 "ነገር ግን እንዳትሴስኑ ሰው ሁሉ በሚስቱ ይወሰን። ሴትም ሁላ በባሏ ትወሰን። ለሚስትም ባሏ የሚገባትን ያድርግላት። እንዲሁ ሚስትም ለባልዋ የሚገባውን ታድርግለት"። ከተጽእኖ ነጻ የሆነ ትዳር ያስፈልጋል። ይህም ማለት ወንዱ የሴቲቱን እሷነቷን ሳይወድ ገንዘቧን ወይም የታላቅ ሰው ዘር ስለተባለች ብቻ ወይም በሌላ ምክንያት ሊያገባት አይገባም። ሴቲቱም የወንዱን እሱነቱን ሳትወድ በሌላ ተጽእኖ (ምሳሌ እድሜየ ሄደ፣ ቤተሰብ አግቢ እያሉ ጨቀጨቁኝ... ወዘተ በማለት) የማትወደውን ሰው ማግባት የለባትም። ሌላው ከተጋቡ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ወይም ከሴቲቱ ችግር ወይም ከወንዱ ችግር መውለድ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ግን ትዳርን መፍታት እግዚአብሔርን እንደመስደብ ይቆጠራል። ልጅን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነውና። ስለዚህ በዚህ ምክንያት ልጅ ባላቸው መቅናትም እርስ በእርስ መጋጨትም አይገባም። ከሕግ ውጭ ግንኙነት ያደረጉ ሰዎች ተቀጥተዋል። ስለዚህ እኛም ከሕግ ውጭ የሆነ ግንኙነት አድርገን ዘላለማዊ ቅጣትን እንዳንቀበል እንጠንቀቅ። ከዚህ ቀደም በማወቅም ባለማወቅም አጥፍተንም ከሆነ ንሥሐ ገብተን ካሁን በኋላ ላለው ሕይወታችን እንጠንቀቅ። ሮሜ.7፣2 "ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና። ባሏ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈታለች"። ስለሚል ከሚስት/ከባል አንዱ ቢሞት 10 ወር ቆይቶ ሌላ ማግባት ይፈቀዳል።1ኛ ቆሮ.7፣8 "ነገር ግን ያላገቡትንና አግብተው የፈቱትን እንደ እኔ ሆነው ቢኖሩ ይሻላቸዋል እላለሁ። መታገሥ ባይችሉ ግን ያግቡ በፍትወት ከመቃጠል ማግባት ይሻላልና" ይላልና።

።

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባል።

ይህን ቀዳሚ ገጽ አድርገህ እኒህን አስሩን ክፍሎች #በእንተ #መርዓት #ወመርዓዊ የሚል ርእስ ሰጥተህ ፒዲኤፍ አዘጋጅተህ ላክልኝማ።

**አዘጋጅ:- መ/ር በትረማርያም አበባው**